# እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማርያም ተብለው የተጠሩ ብዙዎች ሲኖሩ ይህችን ግን ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት ብለን እንጠራታለን።

ማርያም ማለት ፀጋ ወሀብት ፤ ፍጽምት፤ ልዕልት፤ ተላኪተ እግዚአብሔር ወሰብእ፤ መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት ማለት ነው።

አባቷ ቅዱስ እያቄም ይባላል እናቷ ቅድስት ሐና ትባላለች መካን ሆነው ሲኖሩ እግዚአብሔር አምላክ በመጨረሻ ለራሱ እናት እንድትሆነው ከአባቶች ወገብ ጀምሮ ያዘጋጃትን ሴት ልጅ ወለዱ ስሟንም ማርያም ብለው ጠሯት። ወንድምም እህትም የላትም ለወላጆቿ ብቸኛ ናት።

መኃ. 6፥9 "ርግቤ መደምደሚያዬም አንዷት ናት ለእናቷዋ አንዷት ናት ለወለደቻትም የተመረጠች ናት።"

እያቄምና ሐና የወለዷት በስለት ነበር። ስለታቸውም የሚወልዱትን ልጅ በቤተመቅደስ እንዲኖር ለእግዚአብሔር መስጠት። በዚህም መሠረት ድንግል እመቤታችን የ3 ዓመት ህፃን እንደሆነች ወደ ቤተመቅደስ አስገቧት።

መዝ. 44(45)፥10 "ልጄ ሆይ ስሚ እይ ጆሮሽንም አዘንብይ ወገንሽን የአባትሽንም ቤት እርሺ ንጉሥ ውበትሽን ወድዷልና እርሱ ጌታሽ ነውና"

እመቤታችን በቤተመቅደስ 12 ዓመት ኖረች ከዚያም ሰይጣን በአይሁድ አድሮ ከቤተመቅደስ እንድትወጣ አደረጉ ምክኒያታቸውም ድንግል ማርያም እንደ ሌላ ሴት መስላቸው ነው። እርሷ ግን ከሴቶች ሁሉ ንጽህት ናት። ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ ወደ እርሷ ሲመጣ ያላት እንዲህ ነበር።

ሉቃ. 1፥28 "ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት"

ከቤተመቅደስም በወጣች ጊዜ ለእግዚአብሔር የተሰጠች ናትና ከሽማግሌዎች ለአንዱ በአደራ እንድትሰጥ ሆኖ ዮሴፍ የተባለ ቅዱስ ሰው ይጠብቃት ዘንድ ተሰጠች።

በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትዕዛዝ በወጣች ጊዜ ዮሴፍ እመቤታችንን ይዞ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነስቶ ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ ሄደ በዚያም እመቤታችን የዓለምን መድሐኒት ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደች።

## ወላዲተ አምላክ

ድንግል ማርያም እመቤታችን የወለደችው ኢየሱስ እርሱ አምላክ ነው። ቀድሞ በነቢዩ በኢሳይያስ ትንቢት ተነግሮ ነበር።

ኢሳ. 9፥6 "ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር <u>ኃያል አምላክ</u> የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል"

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ከሰማይ ወርዶ ከድንግል የተወለደው የሁላችን ቤዛ ኢየሱስ እኛን ለማዳን ሰው ይሁን እንጂ እርሱ <u>ለዘላለም የተባረከ አምላክ</u> ነው አሜን ይላል - ሮሜ 9፥5

ስለዚህ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ (አምላክን ወለደች) ተብላ ትጠራለች። ይህ ለሌላ ለማንም አይቀጸልም፡ አይባልም።

## እመ ብርሃን

እም ማለት በግዕዙ እናት ማለት ሲሆን ብርሃን ደግሞ በብርሃንነቱ ጨለማን አስወገደ ማለት ዲያብሎስን አራቀ የተባለ ኢየሱስ ነው።

ዮሐ 8፥12 "ደግሞም ኢየሱስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው"

ስለዚህም ነገር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ብርሃን ነኝ ያለ የሆነ ኢየሱስን ወልዳልናለችና እመ ብርሃን (የብርሃን እናት) ተብላ ትጠራለች።

## ቅድስት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሰው ሁሉ ወገን ተለይታ ቅድስት ንጽይት ናት። የእርሷ ቅድስናና የሌሎች ፈጽሞ ግንኙነት የለውም።

ሉቃ. 1፥42 "አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ"

እግዚአብሔር ሰውን በማዳን ዕቅዱ ለእርሱ ሰው መሆን ራሱ ቅድስት አድርጎ ለይቶ በአባቶች ወገብ ሲያስተላልፋት የነበረች ንጽይት ዘር ነበረች። በዚህም ምክኒያት ከጥፋት ዳንን።

ኢሳ. 1፥19 "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆን ገሞራንም በመሰልን ነበር።"

ስለዚህ እመቤታችን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ያልነካት ማለት በአዳምና በሔዋን የደረሰ ለትውልድ ሁሉ የተላለፈ ኀጢአት ፈጽሞ ያልደረሰት ቅድስት የሆነች ናት።

መኃ. 4፥7 "ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው ነውርም የለብሽም"

## ድንግል

እመቤታችን ድንግል ማርያም - ቅድመ ጸኒስ ፣ ጊዜ ጸኒስ፣ ድህረ ጸኒስ ማለት ጌታን ከመጸነሷ በፊት፣ በጸነሰች ጊዜ፣ ከጸነሰች በኋላም ድንግል ናት። ልክ እንዲሁ ፦ ቅድመ ወሊድ ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድህረ ወሊድ ድንግል ናት። ማለት ጌታን ከመውለዷ በፊት፣ በወለደችው ጊዜ ከወለደችው በኋላ ዘላለማዊ ድንግል ናት። ነቢዩም ይህን ድንቅ ምልክት ጌታ ይሰጣችኋል አለ።

ኢሳ. 7፥14 "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፡ እንሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች"

ታላቁ ምልክትና ድንቅ የሆነው ነገር ይህ ነው። እናትነትና ድንግልናን አስተባብራ የያዘች። ተአምሩም ይህው ነው፡ በኅቱም ድንግልና ጌታ ከሷ ተወልዶ ሰው ሆነ።

ነብዩ ሕዝቅኤል የተነበየውም በዚህ ተፈጸመ እንዲህ ብሎ፦ ሕዝ. 44፥1 "…ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበር። እግዚአብሔርም፦ ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል።"

የእመቤታችን ድንግልና በ3 ዓይነት ነው።

1. በኀልዮ (በሐሳብ)
2. በነቢብ (በመናገር)
3. በገቢር (በመሥራት)

በነዚህ በሦስቱም ዓይነት እመቤታችን ኀጢአት አልሰራችም። ለምሳሌ ብዙ ሰዎች ድንግል ሆነው ለእግዚአብሔር ራሳቸውን ሰጥተው የኖሩ አሉ። በሥጋ ድንግል ይሁኑ እንጂ በአስተሳሰባቸው ወይም በንግግራቸው ኀጢአትን መሥራታቸው የማይቀር ነው። እመቤታችን ግን በሐሳብም፣ በመናገርም፣ በማድረግም ፈጽማ ኀጢአትን ያልሰራች የእግዚአብሔር ልዩ መቅደሱ ናት።

## የአክብሮት ስግደትና ምስጋና ለእመቤታችን

እውነተኛ ምዕመናን የአምላክ እናት ለሆነች ለድንግል ማርያም የሚገባትን ክብር ይሰጣሉ። እመቤታችን ድንግል ማርያም የባለሟልነት፣ የመወደድ፣ የመፈራት ልዩ ግርማ አላት። የባለሟልነት ግርማ በሥላሴ ዘንድ፣ የመወደድ ግርማ በመላዕክትና በምእመናን ዘንድ፣ የመፈራት ግርማ በአጋንንትና በመናፍቃን ዘንድ ራዕ. 12፥1 " ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጎናጽፋ ጨረቃ ከእግሮቿ በታች ያላት በራስዋ ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች።" ይህቺ ሴት እመቤታችን ለመሆኗ ቁጥር 5 ላይ "አሕዛብን ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ወንድ ልጅ ወለደች ይላል።

ፀሐይ የተባለ - ኢየሱስ

ጨረቃ የተባሉ - ቅዱሳን

12 ከዋክብት የተባሉት - 12ቱ ሐዋርያት ናቸው - ክብሩ ይህ ነው- አጋንንት ግን ይጠሏታል።

ታዲያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን ለእመቤታችን የምትሰጠው ክብር በመጽሐፍ ቅዱስ በተፃፈው መሠረት ነው። ለምሳሌ መላኩ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ ወደ እርሷም ገብቶ እንዲህ አላት ፦ ሉቃ. 1፥28 "ተፈስሒ ፍሥሕት ኦ ምልዕተ ፀጋ ከእግዚአብሔር ምስሌኪ ቡርክት አንቲ እምአንስት"

እኛም ስናመሰግናት ልክ ከእግዚአብሔር እንደተላከው መልአክ "ደስ ይበልሽ" "ከሴቶች ሁሉ ልዩ የሆንሽ" እያልን እናመሰግናታለን። ይህ ምስጋና በመልአኩ የተጀመረ ሳይሆን የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ነቢያት በትንቢታቸው ስለ እመቤታችን ሳይናገሩ አላለፉም። ቅዱስ ዳዊት በመዝ. 44(45)፥9-13 " በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸፋፍና ንግስቲቱ በቀኝ ትቆማለች ... ለሐሴቦን ንጉሥ ልጅ ሁሉ ክብርዋ ነው።" ብሎ ትንሣኤዋን ሳይቀይር ተናገረ።

በሉቃስ ወንጌልም እንደተጻፈው ራሷ እመቤታችን ከእግዚአብሔር የተወለደ መንፈሳዊ ሕይወት ያለው ትውልድ ለዘላለም እንደሚያመሰግናት ተናግራለች።

ሉቃ. 1፥48 "ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል"

እኛም ትውልድ ነንና የመጽሐፋንም ቃል እንስማለንና ቅድስት እናታችን ድንግል ማርያምን ብፅዕት ብለን ምስጋና እናቀርብላታለን። ምስጋናውም የሚገለጸው በአንደበት በመመስከርና የትህትና ምልክት የሆነውን ስግደት በመስጠት ነው። ስግደቱም የአክብሮት ስግደት ይበላል።

ሉቃ. 1፥4 "ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማህፀንዋ ውስጥ ዘለለ (ሰገደ) - በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት በታላቅ ድምፅም ጮሃ እንዲህ አለች፦ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው"

በዚህ የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የምናስተውላቸው፦

ሀ. የእመቤታችን ድምፅ ኃይል - ፅንሱ ማዘለል

ለ. መንፈስ ቅዱስ የሞላበት ሰው እመቤታችንን ይወዳል - እንደ ኤልሳቤጥ

ሐ. ድንግል ማርያም እመቤታችን ከሰዎች (ከሴቶች) ልዩ መሆንዋ

መ. ኤልሳቤጥና በማኅፀንዋ ያለው ዮሐንስ ለድንግል መስገዳቸው

አንዳንዶች ከዚህ ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ በመሆን ይህንን ክብር ላለመስጠት በትዕቢትና በክህደት ሲወጡ ይታያሉ። ሰዓት አለ ሁሉም ለእመቤታችን የሚንበረከክበትና እግዚአብሔር የተወለደብሽ ከተማ የሚልበት።

ኢሳ. 60፥14 "የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ የእግዚአብሔርም ከተማ የእስራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል።"

## የእመቤታችን አማላጅነትዋ

እግዚአብሔር የመረጣቸው ሁሉ ከተሰጣቸው ጸጋ አንዱ የሰው ልጆችን ከእግዚአብሔር ማማለድ ነው። ከሁሉ በላይ ደግሞ እመቤታችን ለፍጥረት ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት ለሚያምነው ሁሉ እናት እንድትሆን የተሰጠች ልዩ ስጦታችን ናት።

ዮሐ. 19፥27 "ነያ እምከ" "እናትህ እነኋት አለው።" እንዲህ የተባለው የዘብዴዎስ ልጅ ሐዋርያው ዮሐንስ የሥጋ እናት ማለት ወላጅ እናት ነበረችው። እሷም የምትለምነውን አታውቅምና ለልጆቿ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ሞትን ለምና ነበር። ማቴ. 20፥20 "አንድ ነገር እየለመነች ወደርሱ ቀረበች ... ኢየሱስም ግን መልሶ የምትለምኑትን አታውቁም ።" አላቸው። ስለዚህ አምላካችን ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ ለዚህ ለዮሐንስ የመንፈስ እናት፣ የምትለምነውን የምታውቅ እናት ፣ ሞትን ሳይሆን ሕይወትን የምትለምን እናት አስከሞት ድረስ ታምኗልና ሲሰጠው ነው የታየው።

ዛሬም በዚህ ዓለም ያለ ሰው ሁሉ የድንግል እመቤታችንን ምልጃ በመረዳት አምላክ ለሁላችን የሰጣት እናታችን መሆኗን ተረድቶ ወደ እርሷ ይማልድ ዘንድ "ሰአሊ ለነ ቅድስት " ቅድስት ሆይ ለምኝልን ይላት ዘንድ ይገባዋል።

መዝ. 44፥12 የምድር ባለጠጎች አሕዛብ በፊትሽ ይማልላሉ" ከዚህም የተነሳ በኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን ሰው ሁሉ እመቤታችን፣ እናታችን እያለ ወደርሷ እየተማለለ ከልጇ ከወዳጇ ምህረትን ይወርሳል።

መዝ. 86፥5 "እምነ ጽዮን ይብል ሰብእ ወብእሲ ተወልደ በውስቴታ" ሰው እናታችን ጽዮን ይላል በውሷም ሰው ተወለደ።
እኛም እንደ ቅዱስ ዳዊት ፣ እንደ ቅድስት ኤልሳቤጥ እንደ ነቢያትና እንደ ሐዋርያት እናታችን ፣ ሞገሳችን ብንላት እንከብራለን ባንላት እንዋረዳለን። እናታችን ብለን አክብረን እንከብር ዘንድ የአምላክ ፈቃድ ይሁንልን፡ ይደረግልን፡ አሜን!

## ቅዱሳን መላእክት

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት በመጀመሪያ በእሁድ ዕለት ከተፈጠሩት መካከል ቅዱሳን መላዕክት አንድ ክፍል ናቸው - መላእክት የሚዳበስ የሚዳሰስ ግዘፍ አካል የላቸውም መንፈስ ናቸው አንጂ። መዝ. 103(104)፥4 "ዘይሬስዮሙ ለመላእክቲሁ መንፈስ ወላእለ ይትላክዎ ነደ እሳት" "መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል"

አግልሎታቸው

ሀ. ውጎ(ወንዝ) ከመፈሰስ እንደማያቋርጥ መላእክትም ያለ እረፍት ቅዱስ እያሉ እግዚአብሔርን ማመስገን - ኢሳ. 6፥2-4
ለ. የእግዚአብሔርን መልእክት ለሰው ልጅ ማምጣት መሳፍንት 13፥2፣ ሉቃ. 1፥11
ሐ. የሰው ልጆችን ልመና፣ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ማሳረግ፣ መውሰድ ራዕ.8፥1-4
መ. ምሕረትን ለሚያምኑት መዐትን ለከሀዲዎች ማዝነብ

ዘፍ. 19፥16-28 ዳን. 3፥24-30 የሐዋ. 12፥7

የአክብሮት ስግደት ለመላእክት

የእግዚአብሔርን ሕግ የሚጠብቁ ሁሉ ለትዕዛዙ ይገዛሉ። እግዚአብሔር ያከበረውን ያከብራሉ የናቀውን ይንቃሉ። አምላካችን ለቅዱሳን መላዕክት የአክብሮት (የጸጋ) ስግደት እንደሚገባቸው ያስተማረን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እራሱን በማምለክ የጸኑትን ታላላቅ ቅድሳን ምሳሌ አድርጎ ነው። በነዚህ ቅዱሳን ያስተማረን እኛም ራሳችንን ዝቅ በማድረግ እናከብራቸው ዘንድ ነው።

- ዘፍ. 19፥1 ሎጥ ለሁለቱ መላእክት ሰገደ
- ኢያ. 5፥14 ኢያሱ እራሱን ለገለጠለት መልአክ ጌታዬ ብሎ ሰገደ
- መ.ዜና መዋ. 21፥16 ዳዊትና ካህናቱ በአወደ ኦርና ለመልአኩ ሰገዱ
- መሳ. 13፥20 የሶምሶን ወላጆች ለመልአኩ ሰገዱ
- ምንም እንኳን መልአኩ በትሕትና ቢከለክለውም ታላቁ ቅዱስ ዮሐንስ ከአንዴም ሁለት ጊዜ ለመልአኩ ሰገደ ራዕ. 19፥10፣ 22፥8

በተቃራኒው ቅዱሳን መላእክትን አላከብራቸውም ምንድናቸው የሚል ቢኖር ዝምድናው ከዲያብሎስ ጋር ነው።

ራዕ. 12፥7 ዲያብሎስ ከመላእክቱ ጋር ተዋግቶ እንደወደቀ ይነግረናል።

2ኛ ጴጥ. 2፥11-16 "ደፋሮችና ኩሩዎች ሆነው ሥልጣን ያላቸውን ሲሳደቡ አይንቀጠቀጡም ዳሩ ግን መላእክት በኃይልና በብርታት ከእነርሱ ይልቅ ምንም ቢበልጡ በጌታ ፊት በእነርሱ ላይ የስድብን ፍርድ አያመጡም .... የአመጻቸውን ደሞዝ ይቀበላሉ ... ቅንን መንገድ ትተው ተሳሳቱ የባሶርን ልጅ የበለዓምን መንገድ ተከተሉ..."

የባሶር ልጅ በለዓም ማን ነበር? የተቀመጠባት አህያ እንኳ ለመላኩ ክብር ስትሰጥ እርሱ ግን መልአኩን ያላከበረ ያየው ዘንድም ያልቻለ መንፈሱ በባላቅ ገንዘብ የታወረ ከአህያይቱ ያነሰ ጠንቋይ ነበር። ዘኃ. 22፥21-35

## የመላእክት ምልጃና ተራዳኢነት

ከላይ እንዳየነው እግዚአብሔር መላእክት ከፈጠረበት ዓላማ የሰው ልጆችን ለመራዳት፣ ለመጠበቅ ፣ ወደ ገነት ለመምራት ወዘተ.. ነው።

ዘጸ. 23-20 "በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ፣ <u>ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ</u> ያገባህ ዘንድ እነሆ እኔ መልአክን በፊትህ እሰዳለሁ <u>በፊቱ ተጠንቀቁ</u>፣ <u>ቃሉንም አድምጡ</u> ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኅጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና <u>አታስመርሩት</u>"

ዕብ.1፥14 "ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው <u>ለማገዝ የሚላኩ</u> የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?"

ከዚህ የእግዚአብሔር ቃል እንደምንማረው የሰውን ልጆች በምልጃቸው በተራዳኢነታቸው እንዲያገለግሉ መላእክትን የሚልክ ራሱ አምላካችን ነው። መላእክት ለሰው ሲጸልዩ እንዲህ ታይተዋል።

ዘካ. 1፥12 "የእግዚአብሔር መልአክ መልሶ አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ እነዚህ ሰባ ዓመት የተቆጣሃቸውን ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከ መቼ ነው? አለ። እግዚአብሔርም መልሶ ከኔ ጋር ይነጋገር ለነበረው መልአክ በመልካምና በሚያጽናና ቃል ተናገረው።"

ሉቃ. 13-6-9 ጌታችን ምሳሌ መስሎ ሲያስተምር - ፍሬ ያላፈራችው በለስ ጌታዋ ትቆረጥ ሲል ጠባቂዋ ደግሞ ጌታውን ለምኖ ከመቆረጥ ሲያድናት እናያለን። የበለሷ ጌታ ጌታችን ነው፣ በለስ የተባልን የሰው ልጆች ነን፣ ጠባቂ የተባሉ መላእክት ናቸው - መላእክት ስለ እኛ እንደሚጸልዩ በግልጥ ያሳያል - "ጌታዬ ሆይ... በዚች ዓመት ደግሞ ተዋት ... አለው"

### የመላእክት ክብር

ሉቃ. 2፥8 "... እነሆም የጌታ መልአክ ወደነርሱ ቀረበ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ"

ማቴ. 28፥2 "እነሆም የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ"

ሐዋ. 12፥7" እነሆም የጌታ መልአክ ቀረበ በቤቱም ውስጥ ብርሃን በራ"

ራዕ. 18፥1" ታላቅ ሥልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ ከክብሩም የተነሳ ምድር በራች"

## ቅዱሳን ሰዎች

ቅዱሳን ሰዎች የምንላቸው ከሌላው የሰው ልጅ በበለጠ እራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ - ከሰው ወገን ሁሉ የተመረጡ የእግዚአብሔር ምርጥ እቃዎች አለምን የሚያስተምርባቸው የተለዩ አገልጋዮች ናቸው።

ዓለምን የናቁ አምላካቸውን ያወቁ የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር ድንቅ ሥራውን ታላቅ ኀይሉን በእነርሱ ላይ አሳድሮ የጨለማን መጋረጃ አስወግዶ ብርሃንን ይፈነጥቅ ዘንድ የተጠቀመባቸው ከወንድም ከሴትም የተመረጡ አገልጋዮቹ ናቸው። እነዚህም በራሱ የተጠሩና የተዘጋጁ አስቀድሞም የወሰናቸው ናቸው።

ሮሜ. 8፥29 "ልጁ በብዙ ወንድሞች መከከል በኩር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው <u>የልጁን መልክ እንዲመስሉ</u> አስቀድሞ ወሰኗልና አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው።"

ቤተክርስቲያናችን ቅዱሳን ብላ የምታከብራቸው፦

ሀ. ነቢያት

ለ. ሐዋርያት

ሐ. ሰማዕታት በአጠቃላይ ጻድቃን።

ከእግዚአብሔር ቃል እንደምንረዳው አስቀድሞ ለቅድስና የወሰናቸው እግዚአብሔር፣ የጠራቸው እግዚአብሔር፣ ያጸደቃቸው እግዚአብሔር፣ ያከበራቸውም እግዚአብሔር። እኛ ክርስቲያኖች ለቃሉ ተገዢ ነንና የጠራቸውን እንጠራቸዋለን ፣ ያጸደቃቸውን ጻድቃን እንላቸዋለን፣ ያከበራቸውን እናከብራቸዋለን። እንደ ከሀዲያን ቃሉን አንጥስም።

### የልጁን መልክ እንዲመስሉ

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰነ ሲል - ልጁ የተባለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ማቴ. 3-17 "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው።" ስለዚህም ነገር ቅዱሳን የሚመስሉት ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ አለ፦
1ኛ ቆሮ. 11፥1 "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ"

<u>ከሚመስሉበት ዋና ዋናው</u>

የሚመስሉበት ዋናው ነገር የተሰጣቸው ሥልጣንና ጸጋ ይሆናል። ዮሐ. 14፥12 "እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህ የሚበልጥ ያደርጋል።"

በማይታበለው በአምላካችን ቃል መሠረት እግዚአብሔር ለመረጣቸው ጸጋውን አብዝቶ ይሰጣል። በሚቀጥሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት የተሰጣቸውን ይመስሉት ዘንድ ያደላቸውን ክብር እንመልከት።

ሀ. <u>እግዚአብሔር አምላክ ነው</u>

ዘጸ. 20፥2 "እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ"

ሆሴ 13፥4 "ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታውቅም"

የፍጥረት ሁሉ ገዢና ባለቤት የሆነ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ቅዱሳን የጸጋ አማልክት ያደርጋቸዋል። ይህም በማያልቀው ጸጋው የሰጣቸው ክብር ነው።

ዘጸ. 7፥1 "እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፦ እይ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለው።"

ዮሐ. 10፥34 "ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፦ እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ" መዝ. 81፥6

ለ.<u>እግዚአብሔር ምንም አይሳነውም</u>

ዘፍ 18፥14 "በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?" ምንም አይሳነውም። ይህ ምንም የማይሳነው አምላካችን ከሰው ወገን ሁሉ የመረጣቸውን ቅዱሳን በሚለምኑት ሁሉ ምንም እንዳይሳናቸው ነግሮአቸዋል፡ አደርጓቸዋል።

ማቴ. 17፥20 "የሚሳናችሁም ነገር የለም"

ሐ. <u>ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ነው።</u>

ዮሐ. 8፥12 "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ"

አዎ! ጨለማ ሁሉ የራቀበት እውነተኛ ብርሃን ነው። ክርስቶስ ብርሃናችን ነው። እንቅፋትና እሾህ ሁሉ ይርቃል - አባታችን ቅዱስ ዳዊትም ሲዘምር መዝ. 26(27) ፥1 "እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴና ነው።" ይል ነበር። ይህ የዓለም ብርሃን የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅዱሳን እርሱን ይመስሉ ዘንድ የሰጣቸው ጸጋ ብዙ ነውና አንዱ ለዚህ አልጫ ለሆነው ዓለም ጨው እንዲሆኑና በጨለማ ውስጥ ለሚመላለሱ በጸሎታቸው፣ በትምህርታቸው፣ በአማላጅነታቸው ብርሃን ይሆኑ ዘንድ ነው።

ማቴ. 5፥14 "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ"

ልናስተውለው የሚገባው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ - አምላክነቱ፣ ሁሉን ቻይነቱ፣ ብርሃንነቱ ገንዘቡ የሆነ የባህርይው ነው። የቅዱሳን ግን የጸጋ ነው። ለእነሱ ይህንን ስልጣንና ክብር የሰጣቸው ራሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እኒህ ቅዱሳንም በኑሮአቸው፣ በሞታቸው ሁሉ እርሱን የመሰሉ ጻድቃን ናቸው።

<u>የቅዱሳን በረከታቸው</u>

በረከታቸው ለዘላለሙ በእውነት ይደርብንና የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለጻድቃን የሰጣቸው በረከት ሊቆጠርና ሊሰፈር የሚቻል አይደለም።

ማር. 16፥17 "በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፣ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፣ እባቦችን ይይዛሉ፣ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፣ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ"

ይህ እንደሚሆን በእምነት የተመለከተ ነቢዩ ኢዩኤል ቀድሞ በትንቢቱ እንዲህ ብሎ ነበር። "መንፈሴን በሥጋ ለባሹ ሁሉ ላይ አፈሳለሁ" ኢዩ. 2፥28

ይህ ማለት በጠቅላላ የሰው ልጅ ተአምር አድራጊ ይሆናል ማለት ሳይሆን ከላይ እንደተመለከትነው በተመረጡት ቅዱሳን የሚሰራ የእግዚአብሔር ሃይል ነው።

በእነዚህ ቅዱሳን እኛ የምንጠቀመው በረከትን በመውረስ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር የማይፈርስና የማያልፍ የዘላለምን ቃል ኪዳን ከእነርሱ ጋር አድርጓል።

መዝ. 88፥3 "ኪዳነ ተካየድኩ መስለ ሕሩያንየ"

"ከመረጥኩት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ"

በእግዚአብሔርና በተመረጡት መካከል ያለው ቃል ኪዳን እኛን የሚጠቅመው

ሀ. እግዚአብሔር የሰጣቸውን ጸጋና ኃይል በማወቅ

ለ. ከእኛ የተለዩ የልዑል ምርጦች መሆናቸውን በመረዳት

ሐ. የሚገባቸውን ክብር በመስጠት

መ. ዝክራቸውን (መታሰቢአቸውን) በማድረግ

ሠ. በስማቸው ነዳያንን በመርዳት ሌላም በብዙ መንገድ። ይህንን ደግሞ ቤተክርስቲያናችን መመሪያዋ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሆነ ጌታችን በተናገረው ቃል መሠረት ነው። እንዲህ ብሎ፦

ማቴ. 10፥40 "እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል። እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል። ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፣ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም፥"

ይህ የኦርቶዶክስ እምነት የእውነተኛይቱ ክስርስትና ውጤት ነው። ዛሬ ግን ብዙዎች እንኳን ሊቀበሏቸውና በስማቸው ችግረኛን ሊረዱ ቀርቶ ሲሰድቧቸውና ሲያናንቋቸው ማየት የተለመደ ተግባራቸው ነው። እግዚአብሔር ልባቸውን ይመልስ።

ማቴ. 10፥17 "ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰውአችኋል በመብኩራቦቻቸውም ይገርፏችኋልና"

ማቴ. 24፥9 "ስለስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ"

ጌታችን እንደተናገረ በማያምኑ በከሃዲያን ቅዱሳን፣ ጻድቃን እንዲህ ሲጠሉ በምናምነው በእኛ ዘንድ ግን የማያልቅ በረከትን በእነርሱ ላይ ጌታ አድርጓልና።

ምሳ. 10፥6 "በረከት በጻድቅ ራስ ላይ ነው።"

ስለዚህ ይህን በረከት ለማግኘት ከላይ እንዳየነው የቅዱሳንን መታሰቢያ እንጠብቀውና እናደርገው ዘንድ የተሰጣቸውም ክብር በማወቅ እንወዳቸው ዘንድ ክርስቲያን ነን ለምንል ሁሉ የሚገባ ሐቅ ነው።

## የቅዱሳን መታሰቢያቸው

የማይጠፋ ስምን የዘላለም መታሰቢአን ለቅዱሳን ያደረገ እግዚአብሔር እንጂ ሌላ ማንም አይደለ። በነቢዩ በኢሳይያስ መጽሐፍ ስለዚህ ነገር እንዲህ ተጽፏል።

ኢሳ. 56፥5 "በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ የማይጠፋም የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ።"

ከዚህም ቃል የተነሰ ለቅዱሳን በእግዚአብሔር ቤት ላይ የማየጠፋ ለዘላለም የሚሆን የመታሰቢያ ስም ተሰጥቷቸዋል። የእግዚአብሔር ቤት ስንል - ከእዚያ ውስጥ እስቲ እነዚህን እናስብ።

ሀ. ቤተመቅደስ (ቤተክርስቲያን) ማቴ.21፥13 - ቤቴ የጸሎት ቤት ነው።

ለ. ታቦት ዘጸ. 25፥22 - በታቦቱ ሆኜ እነጋግርሃለሁ

ሐ. የሰው ልጅ 1 ቆሮ. 3፥16 - የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ናችሁ

ስለዚህ ቅዱሳን የማይጠፋ የዘላለም መታሰቢያን ስም በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ሰጠኋችሁ ሲል እውነታው ይህ ስም። እኛም ይህን የምናምን ነንና ለቅዱሳን የማይጠፋ ስም እንዲህ ተሰጣቸው ከዚህም የተነሳ -

ሀ. ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ናት ቅዱሳን ደግሞ በቤተክርቲያን በዚህ ስም ተሰጥቶአቸዋል - ምሳሌ፦ የቅዱስ ዮሐንስ የቅ/ጊዮርጊስ ቤ/ክ የቅ/ገብርኤል ቤ/ክ ወዘተርፈ እየተባለ

ለ. ታቦት የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው። ለመታሰቢያ ቅዱሳንም በታቦት ላይ ስም ተሰጥቶአቸዋል - ምሳሌ፦ የቅ/ አስጢፋኖስ ታቦት፣ የተክለሃይማኖት ታቦት፣ የአቡየ ታቦት ነገሰ ወዘተርፈ እየተባለ

ሐ. በክርስቲያን (የሰው ልጆች) ላይ እንዲሁ ቅዱሳን የመታሰቢያ ስም አላቸው- ይህም በሚጠመቁበት ጊዜ ለአንድ ክርስቲያን የሚሰጥ ስም። ምሳሌ ፦ ኃይለ ማርያም፣ ክንፈ ሚካኤል ሰይፈ ገብርኤል ወዘተርፈ

የማይጠፋ መታሰቢያ የዘላለም ስም እሰጣችዋለሁ የተባለው በዚህ ልክ አሁን ከላይ እንዳየነው ነው። ቅዱሳን ለዘላለም በገነት በመንግሥተ ሰማያት ነግሠው ከንጉሰ ነገስት ኢየሱስ ጋር የሚኖሩም ናቸው።

ራዕ. 22፥5 "ለዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ"

መዝ. 111(112) ፥6 "የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል"

ምሳ. 10፥7 "የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው
የኀጥአን ስም ግን ይጠፋል"

## የቅዱሳን አማላጅነታቸው በዚህ ዓለም

አማላጅ ማለት ወደዋናው ባለሙሉ ሥልጣን ሊያቀርብ የሚችል ባለሟል ነው። አማለደ ማለት ለመነ፣ ጸለየ ማለት ነው። ዋናው ባለሥልጣን እርሱ አንድ አምላክ የሆነ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ባላሟሎቹ ደግሞ መረጥኳችሁ፣ ጠራኋችሁ፣ አጸደኳችሁ፣ አከበርኳችሁ ያላቸው ቅዱሳን ናቸው። ይህ የባለሟልነት ሥልጣን የተሰጠቸውም በሰማይና በምድር ንጉሥ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ በጣም በሰፊው የተጻፈ ቢሆንም ከብሉይና ከአዲስ ኪዳን ትንሽ ጥቅሶች እንመልከት።

### በብሉይ ኪዳን

ዘፍ. 20፥7 "ነቢይ ነውና ስለ አንተም ይጸልያል ትድናለህም"

ዘጸ. 8፥8 "ፈርዓንም ሙሴንና አሮንን ጠርቶ ጓጉነቸሮቹን ከኔ ከሕዝቤም እንዲያርቅ ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ" ብሏቸዋል።

ዘጸ. 32፥10-14 እስራኤል ኀጢአትን ሠሩ ሙሴ ግን ስለነሱ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ (አማለደ) ሊያጠፋቸው የነበረው እግዚአብሔርም በሙሴ ልመና ራራ።

መ.ነገ. ቀዳ 13፥1-6 ንጉሥ ኢዮርብዓም የእግዚአብሔር ሰው የሆነ ነቢዩን በናቀ ጊዜና ሊያሲዘው እጁን በዘረጋ ጊዜ እጁ ደረቀች - ከዚያም ነቢዩን ተማጸነ ወደ እግዚአብሔርም ጸልይልኝ አለው። "የእግዚአብሔርም ሰው እግዚአብሔርን ለመነ የንጉስም እጅ ወደ እርሱ ተመለሰች እንደቀድሞም ሆነች።"

ኢዮብ 42፥8 "ባርያዬም ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል እኔም እንደ ስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ" ብሏል እግዚአብሔር።

ኤር. 42፥1-6 ሕዝቡ ሁሉ ተሰብስበው ወደ ነቢዩ ኤርምያስ መጥተው ልመናችን በፊትህ ትድረስ እባክህ አምላክህ እግዚአብሔር የምንሄድበትን መንገድና የምናደርገውን ነገር ያሳየን ዘንድ ስለእኛ፣ ስለዚህ ቅሬታ ሁሉ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይ አሉት። እርሱም ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ አላቸው።

### በአዲስ ኪዳን

ያዕ. 5፥16 " የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች፣"

2ቆሮ 5፥20 "በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ ። እንግዲህ እግዚአብሔር

በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን።”

- እዘህ ጥቅስ ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ  ትረጉም ላይ የፊደል ለውጥ አለ።  የቅዱሳንን አማላጅነት እንሰርዛለን ብለው ትልቅ ስህተት ስረተዋል ይከውም እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ የሚለውን እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ብለው ፊደል ‘ለ’ ን ወደ ‘ል’ ለውጠው አምላክ እግዚአብሔርን  አማላጅ ብለውታል። ለስም አጠራሩ ክብር ይግባውና እኛ ግን በእውነቱ እንሄዳለን።

ዮሐ. 9፥36-43 በኢዮጴ የነበሩ ክርስቲያኖች ጣቢታ የሚሏት ዶርቃ በሞተች ጊዜ ወደ ልዳ አግ ሄደው ቅዱስ ጴጥሮስን ጣቢታን ከሞት እንዲያስነሳለቸው ሲለምኑት ተጽፎአል እርሱም ሄዶ ተንበርክኮ ጸለየ ህያውም አድርጎ በፊታቸው አቆማት። ሰዎቹ ጴጥሮስን ለመኑት እርሱ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር አማልዶ ልጅቷን አስነሳት።

የሐዋ 3፥1-10 መልካም በሚሏት በመቅደስ ደጅ የሚቀመጠውን ሽባ ቅዱስ ጴጥሮስና ዮሐንስ ወዳእኛ ተመልከት ብለው ባለቸው ጸጋ ሲፈውሱት ሲፈቱት  እናያለን።

ማቴ. 15፥21-28 ሴት ልጇ በጋኔን ትሰቃይባት የነበረች አንዲት ከነናዊት ጌታን ልጇን እንዲፈውስላት በለመነች ጊዜ ዝም ቢላት ደቀመዛሙርቱ  ናቸው ጌታ ሆይ አሰናብታት ባሉት ጊዜ ያናገራትና ልጇን የፈወሰላት።  ማማለድ ማለት ይህ ነው። እንግዲህ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን በትንሹ እንደተመለከትነው የቅዱሳን ጸሎት ወይም አማላጅነታቸው ጥርጥር የሌለው የእግዚአብሔር እውነት ነው።  አንዳንድ ይህ ምስጢር ያልገባቸው ሰዎች እኔ ራሴ በቀጥታ ወደ አምላኬ እጸልያለሁ አማላጅ አያስፈልገም ሲሉ  ይደመጣሉ።  በመጀመሪያ ማንኛውም ሰው ቀጥታ ወደ አምላኩ ለመጸለይ ይችላል የከለከለ የለም። ዳሩ ግን አማለጅ የሚያስፈልገው፦

ሀ. እግዚአብሔር የማማለድን ፣ የማስታረቅን ቃል ኪዳን ለቅዱሳን ስለሰጠ

ለ. በአብዛኛው ከነሱ ይልቅ እኛ በኃጢአት ስለምንወድቅ

ሐ. በቅድስና ህይወት ቅዱሳን ጻድቃን ከኛ ስለሚበልጡ

መ. የእግዚአብሔር ባለሟሎች ከሰው ወገን ሁሉ ለይቶ ስለመረጣቸው

መዝ. 33፥15 የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን ጆሮዎቹም ወደ ጩከታቸው ናቸውና”

ለዚህም ነው ከላይ በጥቅሶቹ እንዳየነው ሁሉ ከእግዚአብሔር ምህረትን የፈለገ ሁሉ ወደቅዱሳን፣ ወደጻድቃን፣ ወደነቢያት ፣ ወደ ሐዋርያት፣ ወደሰማዕታት እየሄደ እባካችሁ ጸልዩልኝ፣ ጸልዩልን የሚለው  ራሱ መጸለይ አቅቶት አይደለም እርዳታን ሽቶ እንጂ ያውም ከተመረጠ ባለሟል።  እርሱም እራሱ ቀጥታ ይጸልያል።

## የቅዱሳን አማለጅነታቸው ከዚህ ዓለም በኋላ

እግዚአብሔር ለቅዱሳን የሰጠው ክብርና ኃይል ጊዜያዊ የሆነ፣ ዕድሜ ሚገድበው፣ ቦታ የሚከልለው፣ አድማስ የሚሸፍነው የዚህ አለም ሞት የሚያሸንፈው አይደለም።  ይህ ግን ያልገባቸው ሰዎች ቀድሞ ፍጹም ቅዱሳን ማማለድ አይችሉም ይሉ ነበር። አሁን ደግሞ ያመጧት በህይወት እያሉ ያማልዳሉ ከሞቱ በኋላ ግን አያማልዱም የሚል ነው።  ይህንንም እያሉ ያሉበት የእግዚአብሔር ምስጢር ገብቷቸው ሳይሆን ራሳችን እናማልዳለን (እንጸልያለን)  ስለሚሉ ለዚያ ትዕቢታቸው ካባ ነው።

ለመሆኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ምን ብሎ ነበር?

ዮሐ. 11፥25 “ኢየሱስም ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል” እንደውም ቅዱሳን ከዚህ ዓለም ሲለዩ ወደበለጠ ክብርና አክሊል ይሄዳሉ አንጂ ወደ ድካም አይጓዝም።

2ጢሞ. 4፥7 “ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል” ስለዚህም ቅዱሳን ሞታቸው ክብራቸው ነው። እግዚአብሔርም ወደሚበልጥ ክብር ያሸጋግራቸዋል።

መዝ. 115(116) ፥6 “ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር”

“የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው።”

ይህንን የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ማመን ያልፈለጉ ሰዎች “ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ” እንደሚባለው የአበው ብሂል የጻድቃንን ለጎጥአን